ACES
Achieving Collegiate Excellence & Success

# የማመልከቻ ስምምነት ቅጽ

ይህ የማመልከቻ ስምምነት ቅጽ ታትሞ፣ ተፈርሞበት እና የልጅዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኝ የኤሲኢኤስ የተማሪ ስኬት አስተባባሪ **ጥር 9 ቀን 2026 ዓ.ም** በፊት መቅረብ አለበት።

ለኤሲፒኤስ ፕሮግራም አጋሮች ከኤሲፒኤስ ፕሮግራም ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የአይኢፒ/504 እቅድ መረጃ፣ ትራንስክሪፕቶች፣ ገንዘብ ነክ እርዳታ መረጃዎች እና ሌሎች የአካዳሚክ መረጃዎችን ጨምሮ በእኔ ወይም በልጄ የትምህርት መዛግብት ውስጥ ያሉትን መረጃዎች እንዳስፈላጊነታቸው እንዲገመገሙ እና እንዲጋሩ ፈቃዴን እሰጣለሁ።

የመግባቢያ ዘዴ ስምምነት፥ እኛ የምንጠቀምባቸው የመግባቢያ ዘዴዎች፣ ዩኤስ ሜይል፣ ኢሜይል፣ የስልክ ጥሪዎች፣ የጽሁፍ መልእክቶች፣ የቪዲዮ ኮንፈረንስ (ለምሳሌ ዙም) እና የማህበራዊ መገናኛ ሚዲያዎችን ሲሆኑ በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም። ለኮሌጅ እና ለቀጣይ የህይወት ጉዞ ተማሪዎችን ዝግጁ ለመሆን እንዲችሉ ፕሮግራማችን ተማሪዎችን ለመመልመል እና ለማዘጋጀት ወሳኝ ስለሆኑ እነዚህን የተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎች ከወላጅ/አሳዳጊ እና ተማሪ ጋር ለመግባባት በተቻለ መጠን እንድንጠቀምባቸው በአክብሮት የእርስዎን ፈቃድ እንጠይቃለን። **ይህንን ቅጽ በመፈረም፣ ለኤሲኢኤስ ፕሮግራም የሚያቀርቡት ፈቃድ እነዚህን የተለያዩ የመገናኛ መንገዶች በመጠቀም ወላጆችንን፣ አሳዳጊዎችን እና ተማሪዎችን ከኤሲኢኤስ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ለማግኘት እንድንችል ነው።**

*የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ኤሲኢኤስ ፕሮግራም ውስጥ ለመቆየት ከፈለጉ የሁለተኛ ዳረጃ ትምህርት የመጨረሻ አመት ከመድረሱ በፊት ባለው የበጋ / ሰመር/ ወቅት የሚካሄደውን የሞንትጎመሪ ኮሌጅ የተማሪዎች የመመዝገቢያ እና የመቀበያ ሂደት ጠብቀው መመዝገብ ይኖርባቸዋል። የመጨረሻው የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አመት ከመጀመሩ በፊት የሚደረገውን የሞንትጎመሪ ኮሌጅ የተማሪዎች የመቀበያ ሂደት ተከትለው መመዝገብ የማይችሉ ከሆነ ተሳታፊዎች እራሳቸውን ከፕሮግራሙ ማግለል ይችላሉ። በተጨማሪም በሞንትጎመሪ ኮሌጅ የሚካሄደውን የተማሪዎች የምዝገባ/ቅበላ ሂደትን አክብረው የሚጠበቅባቸውን ምላሽ የማይሰጡ ከሆነም ተሳታፊዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የመጨረሻ አመት ከመግባቱ በፊት በራሱ በፕሮግራሙ ውሳኔ ከፕሮግራሙ እንዲወጡ ሊደረግ ይችላል።*

የኤሲኢኤስ ፕሮግራም ሁሉንም ማመልከቻዎች በተናጠል የማየት እና ተጨማሪ የግል እና ትምህርታዊ ሁኔታዎችን በማካተት የመጨረሻውን የመግቢያ ውሳኔ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው። የኤሲኢኤስ ፕሮግራም ለሌላ አካል ግለሰብን የሚገልጽ መረጃ አያካፍልም፤ ወይም ያለተማሪው ወላጅ ቅድመ ፈቃድ ለሌላ አላማ መረጃዎችን አያጋራም።

ይህ የማመልከቻ ስምምነት ቅጽ የኤሲኢኤስ ፕሮግራም ማመልከቻ አካል ሲሆን ነገር ግን የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲስ ኦፍ ሼዲ ግሮቭ ባሉ ማንኛውም ፕሮግራሞች ማመልከቻ አይደለም።

ማመልከቻውን ማስገባት ወደ ኤሲኢኤስ ፕሮግራም ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት ላይ ዋስትና እንደማይሰጥ ተረድቻለሁ።

ተማሪ ኤምሲፒኤስ መታወቂያ ቁጥር፥ ____________________

ተማሪ ስም፥ ____________________ ወላጅ ጠባቂ ስም፥ ____________________

ተማሪ ፊርማ፥ ____________________ ወላጅ ጠባቂ ፊርማ፥ ____________________

ቀን፥ ____________________ ቀን፥ ____________________

ወላጆች/ጠባቂዎች፥ ስለ ኤሲኢኤስ ፕሮግራም ያሉትን ሁሉንም ግንኙነቶች እርስዎ እና ልጅዎ እንደሚቀበሉ ለማረጋገጥ እባክዎትን የሚከለተለውን መረጃ ያቅርቡ።

የመኖሪያ አድራሻ፥ ____________________

ከተማ፥ ____________________ ስቴት፥ __________ ዚፕ ኮድ፥ ____________________

ወላጅ የእጅ ስልክ፥ ____________________ ወላጅ ኢሜይል፥ ____________________

**በኢሲኢኤስ ፕሮግራም ለመሳተፍ ምንም ወጪ አይጠይቅም።**